የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሁለተኛ ዓመት ቁጥር ፴
አዲስ አበባ — ሰኔ ፳፰ ቀን ፲፱፻፹፰

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

2nd Year No. 30
ADDIS ABABA – 5th July, 1996

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፵/፲፱፻፹፰ ዓ.ም.
የአነስተኛ ብድር አቅራቢ የገንዘብ ድርጅቶች ፈቃድ አሰጣጥና ቁጥጥር አዋጅ ........................................ ገጽ ፪፻፵፭

## CONTENTS

Proclamation No. 40/1996
Licensing and Supervision of Micro Financing Institutions Proclamation ................................ Page 245

### አዋጅ ቁጥር ፵/፲፱፻፹፰

### ለአነስተኛ ብድር አቅራቢ የገንዘብ ድርጅቶች ፈቃድ ስለመስጠትና ሥራቸውን ስለመቆጣጠር የወጣ አዋጅ

የአነስተኛ ብድር አቅራቢ የገንዘብ ድርጅቶችን እንቅስቃሴ በኢትዮጵያ የገንዘብና የፋይናንስ ፖሊሲዎች ውስጥ ለማካተት የሚያስችል ሕጋዊ ሥርዓት ሊዘረጋ ስለሚገባ ፤

በሀገሪቱ በሥራ ላይ የዋሉት የገንዘብና የባንክ ሕጎች ዝቅተኛ የገጠር ገበሬዎችንና በሌሎች አነስተኛ የምርትና አገልግሎት ሥራ የተሰማሩ ሰዎችን የብድር ፍላጎት ለማሟላት የሚችሉ አነስተኛ ብድር አቅራቢ የገንዘብ ድርጅቶችን መቋቋም የማያመቻቹ በመሆኑ ፤

ለአነስተኛ ብድር አቅራቢ የገንዘብ ድርጅቶች ፈቃድ ስለመስጠትና ሥራቸውንም ስለመቆጣጠር የሚደነግግ ሕግ ማውጣት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭ (፩) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

### ክፍል አንድ

### ጠቅላላ

፩· አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ " የአነስተኛ ብድር አቅራቢ የገንዘብ ድርጅቶች ፈቃድ አሰጣጥና ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር ፵/፲፱፻፹፰» ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

### PROCLAMATON NO. 40/1996

### A PROCLAMATION TO PROVIDE FOR THE LICENSING AND SUPERVISION OF THE BUSINESS OF MICRO FINANCING INSTITUTIONS

WHEREAS, it needs to provide for a legal regime that brings the activities of micro financing institutions within Ethiopia's monetary and financial policies;

WHEREAS, the monetary and banking laws in force do not provide for micro financing institutions catering for the credit needs of peasant farmers and others engaged in small-scale production and service activities;

WHEREAS, it has become necessary to legislate on the licensing and supervision of the business of micro financing institutions;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55(1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

### PART ONE

### *General*

1. *Short Title*

This Proclamation may be cited as the "Licensing and Supervision of Micro Financing Institutions Proclamation No. 40/1996."

ያንዱ ዋጋ / Unit Price } 3·40

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ·ሣ·ቁ· ፹ሺ፩
Negarit G.P.O.Box 80,001

፪· ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፣

፩· " ባንክ" ማለት የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ነው፣

፪· " ኩባንያ" ማለት በንግድ ሕጉ አንቀጽ ፫፻፬ በተሰጠው ትርጉም መሠረት የተቋቋመ፣ አክስዮኑ በሙሉ በኢትዮጵያ ዜጎች እና/ወይም ሙሉ በሙሉ በኢትዮጵያ ዜጎች ባለሀብትነት በተቋቋሙ ድርጅቶች የተያዘ፣ በኢትዮጵያ ሕግ መሠረት የተመዘገበና ዋና መሥሪያ ቤቱ በኢትዮጵያ ውስጥ የሆነ የአክስዮን ማኅበር ነው፣

፫· " አነስተኛ ብድር የማቅረብ ሥራ" ማለት መጠናቸው በባንኩ የሚወሰን ብድሮችን በጥሬ ገንዘብ ወይም በዓይነት ለገጠር ዝቅተኛ ገበሬዎች ወይም በከተማ አነስተኛ የምርትና አገልግሎት ሥራ ላይ ለተሰማሩ የማቅረብ እንቅስቃሴ ነው፣

፬· "አነስተኛ ብድር አቅራቢ የገንዘብ ድርጅት" ማለት በገጠርና በከተማ አካባቢዎች አነስተኛ ብድር የማቅረብ ሥራ እንዲያካሂድ በዚህ አዋጅ መሠረት የተፈቀደለት ኩባንያ ነው፣

፭· "አባላት" ማለት በአነስተኛ ብድር አቅራቢ የገንዘብ ድርጅት ውስጥ የማቋቋሚያ አክስዮን የገዙ ወይም በድርጅቱ የተዘጋጀ ማናቸውም ዓይነት የአባልነት ስምምነት ተፈራራሚዎች ናቸው፣

፮· "የቡድን ዋስትና" ማለት ከመካከላቸው በማንኛውም አባል ላልተ[illegible] ብድር የተበዳሪዎች ቡድን አባላት በአንድነትና በነጠላ ባለእዳ ለመሆን ግዴታ የሚገቡበት የዋስትና ስልት ነው፣

፯· "ቁጠባ" ማለት የአነስተኛ ብድር አቅራቢ የገንዘብ ድርጅት አባላት የሚያስቀምጡት ሊወጣ የማይችል የግዴታ ቁጠባ ወይም መደበኛ ቁጠባ ነው፣

፰· "ተቀማጭ " ማለት በሂሳቡ ባለቤት በማናቸውም ጊዜ በከፊል ወይም በሙሉ ሊወጣ የሚችል መደበኛ ወይም መደበኛ ያልሆነ ቁጠባ ነው፣

፱· "ዲሬክተሮች" ማለት የአነስተኛ ብድር አቅራቢ የገንዘብ ድርጅት የቦርድ አባላት ናቸው።

፫· ዓላማና ተግባር

፩· የአነስተኛ ብድር አቅራቢ የገንዘብ ድርጅቶች ዓላማ ከፍተኛ መጠኑ በባንኩ የሚወሰን ብድር በጥሬ ገንዘብ ወይም በዓይነት መስጠት ነው።

፪· አነስተኛ ብድር አቅራቢ የገንዘብ ድርጅት በዚህ አዋጅ ውስጥ በተደነገጉት ሁኔታዎች መሠረት፣ የሚከተሉትን ሥራዎች በሙሉ ወይም በከፊል ሊሠራ ይችላል፣

ሀ) የቁጠባ ገንዘብ እንዲሁም፣ በተጠየቀ ጊዜ የሚከፈልና በጊዜ ገደብ የሚከፈልን ጨምሮ፣ ተቀማጭ ገንዘብ መቀበል፣

ለ) በኢትዮጵያ ውስጥ ተከፋይ የሚሆኑ የሃዋላ ወረቀቶች ማውጣትና መቀበል፣

*2. Definitions*

In this Proclamation, unless the context otherwise requires:

1) "Bank'' means the National Bank of Ethiopia;

2) "Company'' means a share company, as defined under Article 304 of the Commercial Code, the capital thereof owned fully by Ethiopian nationals and/or organizations wholly owned by Ethiopian Nationals and registered under the laws of, and having its head office in, Ethiopia;

3) "Micro financing business'' means an activity of extending credit, in cash or in kind, to peasant farmers or urban small entrepreneurs, the loan size of which shall be fixed by the Bank;

4) '"Micro financing institution''means a company licensed under this Proclamation to engage in micro financing business in rural and urban areas;

5) "Members'' means the shareholders of a micro financing institution or signatories to any type of membership arrangement created by such institution;

6) "Group guarantee'' means a guarantee mechanism whereby a group of borrowers undertake to be liable jointly or severally to defaulted loan of any one of them;

7) "Savings'' means non-withdrawable mandatory or regular savings of members of a micro financing institution;

8) "Deposits'' means any regular or irregular savings which may be withdrawn partially or totally at any time by the account holder;

9) "Directors'' means members of the board of a micro financing institution.

*3. Purpose and Duty*

1) The purpose of micro financing institutions is granting credit, in cash or in kind, the maximum amount of which shall be determined by the Bank.

2) Subject to conditions set under this Proclamation, a micro financing institution may carry out some or all of the following activities:

(a) accepting savings as well as demand and time deposits;

(b) drawing and accepting drafts payable within Ethiopia;

ሐ) በንብረቱ ዋስትና ወይም በሌላ አኳኋን ለድርጅቱ ሥራ የሚውል ገንዘብ መበደር፣

መ) ዓላማቸው ገቢ ማስገኘት የሆነ እንደ ግምጃ ቤት ሰነዶች ያሉ የንግድ ወረቀቶችን መግዛት፣

ሠ) ሥራውን የሚያከናውንባቸውን ሕንፃዎች ጨምሮ ማናቸውንም የሚንቀሳቀስና የማይንቀሳቀስ ንብረት በባለቤትነት መያዝ፣ መንከባከብና ለሌሎች ማስተላለፍ፣

ረ) ለደንበኞቹ የምክር አገልግሎት መስጠት፣

ሰ) በከተማና በገጠር በአነስተኛ ሥራ ላይ ለተሰማሩ ወገኖች ገቢ የሚያስገኙ ፕሮጀክቶችን ማበረታታት፣

ሸ) ለተበዳሪዎች የሥራ አመራር፣ የገበያ ፣ የቴክኒክና የአስተዳደር ምክር መስጠትና በነዚህም መስኮች አገልግሎት እንዲያገኙ መርዳት፣

ቀ) አነስተኛ ብድር ለማቅረብ ሥራ ዓላማ የሚውል ገንዘብ ማስተዳደር፣ እና

በ) በተለምዶ በአነስተኛ ብድር አቅራቢ የገንዘብ ድርጅቶች የሚሠሩ ሌሎች ሥራዎችን መሥራት።

## ክፍል ሁለት
## ለአነስተኛ ብድር አቅራቢ የገንዘብ ድርጅቶች ፈቃድ ስለመስጠት

### ፬· አነስተኛ ብድር የማቅረብ ሥራ ለማካሄድ ስለሚያስችሉ ሁኔታዎች

፩· አነስተኛ ብድር የማቅረብ ሥራ ለማካሄድ ከዚህ የሚከተሉት ሁኔታዎች መሟላት አለባቸው፣

ሀ) ከባንኩ ፈቃድ ማግኘት፣

ለ) በኩባንያ ቅርጽ መቋቋም፣

ሐ) በባንኩ የተወሰነውን ዝቅተኛ መነሻ ካፒታል በባንክ ማስቀመጥ፣ እና

መ) ዲሬክተሮችና ሌሎች ኃላፊዎች ባንኩ የሚያወጣቸውን መመዘኛዎች መጥነው መገኘት።

፪· አዲስ ዓይነት የሆኑ ሌሎች ገንዘብ አስተላላፊ አካላት አነስተኛ ብድር በማቅረብ ሥራ ላይ እንዲሳተፉ ለማስቻልና ከዚህ አዋጅ ዓላማ ጋር ለሚዛመድ ምክንያት የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ማናቸውም ድንጋጌ በአመልካቹ ላይ ተፈጻሚ እንዳይሆን ባንኩ የውሳኔ ሀሳብና አስተያየት ለሚኒስትሮች ምክር ቤት አቅርቦ ያስወስናል።

### ፭· ተጨማሪ ሁኔታዎችን ስለመደንገግ

፩· ፈቃድ ከመሰጠቱ በፊት መሟላት ያለባቸውን ማናቸውንም ተጨማሪ ሁኔታዎች ባንኩ በየጊዜው በሚያወጣቸው መመሪያዎች ሊደነግግ ይችላል።

፪· ባንኩ ከፈቃድ ጋር የተያያዙ ዝርዝር ሁኔታዎችን ለመለወጥ ወይም ለማሻሻል ሲፈልግ ለውጡን ወይም ማሻሻያውን ሥራ ላይ ለማዋል ካሰበበት ዕለት ፵፭ ቀናት አስቀድሞ ለሚመለከታቸው አነስተኛ ብድር አቅራቢ የገንዘብ ድርጅቶች ያሳውቃል።

(c) borrowing money for its business purposes against the security of its assets or otherwise;

(d) purchasing such income generating financial instruments as treasury bills;

(e) acquiring, maintaining and transferring of any movable and immovable property including premises for carrying out its business;

(f) providing counseling service to its clients;

(g) encouraging income generating projects for urban and rural micro-operators;

(h) rendering managerial, marketing, technical and administrative advice to borrowers and assisting them to obtain services in those fields;

(i) managing funds for micro financing business; and

(j) engaging in other activities customarily undertaken by micro financing institutions.

## PART TWO
## *Licensing of Micro Financing Institutions*

### *4. Conditions Required to Engage in Micro Financing Business*

1) To carry out micro financing business, the following conditions shall be fulfilled:

(a) obtain a license from the Bank;

(b) be formed as a company;

(c) deposit with a bank the minimum initial capital required by the Bank; and

(d) that the directors and other officers meet requirements set by the Bank.

2) The Council of Ministers may, upon recommendation by the Bank, exempt an applicant from the requirements of any of the provisions of sub-Article (1) of this Article inorder that other innovative financial intermediaries engage in micro financing business and for other causes consistent with the objective of this Proclamation.

### *5. Prescribing Additional Conditions*

1) The Bank may issue directives at any time and prescribe additional conditions to be complied with before a license is issued.

2) Where the Bank intends to change or vary the terms and conditions attached to a license, it shall notify the concerned micro financing institutions of such intentions forty-five (45) days before the date it proposes to carry same into effect.

፮· ፈቃድ እንዲሰጥ ስለሚቀርብ ማመልከቻ

፩· አነስተኛ ብድር የማቅረብ ሥራ ለማካሄድ እንዲፈቀድ የሚቀርብ ማመልከቻ የሚከተሉትን መያዝ ይኖርበታል፤

ሀ) ሥራው ሊካሄድ የታሰበበትን አካባቢ (የዋና መሥሪያ ቤቱንና የቅርንጫፎቹን አድራሻ ማመልከት)፤

ለ) የመሥራቾቹን ስም፣ የሥራ መስክ፣ የመኖሪያ አድራሻና ዜግነት፣

ሐ) ድርጅቱ የተቋቋመበትን ቅርጽ ዓይነት፣

መ) ድርጅቱን ለመመሥረት የተደረገውን ስምምነት፣

ሠ) ለድርጅቱ ሊሰጥ የታቀደውን ስያሜ፣

ረ) የእያንዳንዱን መሥራች አባል፣ የታሳቢ ዲሬክተሮችና፣ የኃላፊዎችን የሕይወት ታሪክ መረጃ፣

ሰ) በጥሬ ገንዘብና በዓይነት የተደረገውን መዋጮ የድርሻ መጠን እና በዓይነት የተደረገውን መዋጮ አገማመት፣

ሸ) ድርጅቱ ሊሠራቸው ያቀዳቸውን ተግባሮችና እነዚህኑም ለማከናወን አመልካቹ ሊጠቀምበት ያቀዳቸው ሁኔታዎች፣ እና

ቀ) ባንኩ እንዲቀርብለት የሚጠይቃቸው ሌሎች አግባብነት ያላቸው መረጃዎች።

፪· ፈቃድ እንዲሰጠው የሚጠይቅ አመልካች ማመልከቻውን በሚያቀርብበት ወቅት ባንኩ የሚወስነውን የሠነድ መመርመሪያ ክፍያ ይከፍላል።

፫· ፈቃድ የተሰጠው አመልካች ፈቃዱ ከተሰጠው ጊዜ አንስቶ በአሥራ ሁለት (፲፪) ወራት ውስጥ ሥራውን መጀመር ይኖርበታል።

፬· ከባንኩ በቅድሚያ ይሁንታ ሳያገኝ ማናቸውም አነስተኛ ብድር አቅራቢ የገንዘብ ድርጅት ከተፈቀደለት አካባቢ ውጪ ለመስራት አይችልም።

፭· ማናቸውም አነስተኛ ብድር አቅራቢ የገንዘብ ድርጅት ባንኩ የሚወስነውን ዓመታዊ የፈቃድ ማደሻ ክፍያ ይከፍላል።

፯· ሥራ እንዲጀመር ስለመፍቀድ

ማናቸውም አነስተኛ ብድር አቅራቢ የገንዘብ ድርጅት ሥራውን ከመጀመሩ በፊት ባንኩ በሚያወጣቸው መመሪያዎች የተመለከቱ ሁኔታዎችን እንዲያሟላ ሊጠየቅ ይችላል።

፰· ፈቃድ ከሌላቸው ድርጅቶች ገንዘብና የሚተላለፉ የገንዘብ ሠነዶችን ስለማስመለስ

ማንኛውም ሰው በዚህ አዋጅ መሠረት የሚካሄዱ ሥራዎችን ያለፈቃድ ከሠራና በዚሁ ድርጊት አማካይነት የተቀበለው ገንዘብ ወይም ንብረት ካለ ባንኩ ይህ ገንዘብና ንብረት ምን ሊደረግ እንደሚገባ ትዕዛዝ እንዲሰጥለት ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ለማመልከት ይችላል። ፍርድ ቤቱም ገንዘቡና ንብረቱ ለአስቀማጮች ወይም ለባለንብረቶች በአፋጣኝና በተቀላጠፈ መንገድ እንዲመለስ የሚያስችል ትዕዛዝ ይሰጣል።

፱· ፈቃድ ስለመሠረዝ

አነስተኛ ብድር አቅራቢ የገንዘብ ድርጅት ከዚህ በሚከተሉት ማናቸውም ምክንያቶች ፈቃዱ በባንኩ ሊሰረዝበት ይችላል ፤

፩· ፈቃድ በተሰጠው በአሥራ ሁለት (፲፪) ወራት ውስጥ ሥራውን ሳይጀምር ሲቀር ፤

፪· ሥራውን ሲያቆም ፤

፫· የመክሰር ውሳኔ ሲሰጥበት ወይም እንዲፈርስ ሲወሰን ፤

*6. Application for License*

1) An application for license to carry out micro financing business shall contain the following:

(a) the prospective place of operaiton (indicating that of the head office and branches);

(b) the name, occupation, residence and nationality of the founders;

(c) form of organization of the undertaking;

(d) memorandum of association of the undertaking;

(e) proposed name of the undertaking;

(f) biographical data on each of the founders, proposed directors and officers;

(g) the proportion of contribution in cash and in kind and the manner of valuation of contribution in kind;

(h) the proposed transactions and operations of the undertaking as well as the manner for carrying out same; and

(i) such other relevant information as the bank may require.

2) An investigation fee, prescribed by the Bank, shall be paid at the time of submitting the application for license.

3) An applicant issued with a license shall commence operations within 12 (twelve) months from the date thereof.

4) No micro financing instituion shall, without the prior consent of the Bank, operate outside the area for which it has been issued with a license.

5) Every micro financing institution shall pay such annual license renewal fee as the Bank may prescribe.

*7. Authorization of Commencement of Operation*

Any micro financing institution may, before commencing operations, be required to meet certain conditions prescribed in a directive to be issued by the Bank.

*8. Recovery of Monies and Securities Received by unlicensed undertakings*

Where any unlicensed person undertakes activities carried out pursuant to this Proclamation, and holds monies or property obtained through such act, the Bank may apply to the Federal High Court for orders in respect of the disposition of same; the High Court shall give orders for the speedy and efficient return of such monies or property to the depositors or owners thereof.

*9. Revocation of License*

The license of a micro financing institution may be revoked by the Bank for any of the following reasons:

1) where it fails to commence operations within a period of 12 (twelve) months following the issuance of license;

2) where it ceases to carry on its activity;

3) where it is declared bankrupt or decided that it be liquidated;

፬· ባንኩ በቅድሚያ በጽሑፍ ሳይፈቅድ ከሌላ አነስተኛ ብድር አቅራቢ የገንዘብ ድርጅት ወይም ባንክ ጋር ሲዋሃድ፣ ወይም

፭· በተሳሳተ መረጃ ላይ ተመስርቶ የተመዘገበ መሆኑ ሲረጋገጥ ።

፲· <u>እንደገና ለመመዝገብ ስለሚቀርብ ማመልከቻ</u>

፩· አነስተኛ ብድር አቅራቢ የገንዘብ ድርጅት የሚያንቀሳቅሰው የቁጠባ ገንዘብ ብር ፩ ሚሊዮን (አንድ ሚሊዮን ብር) ሲደርስ እንደገና ለመመዝገብ ማመልከት አለበት።

፪· ድርጅቱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ሲያመለክት፣ ባንኩ ባወጣቸው መመሪያዎች ውስጥ የተጠቀሱ ተጨማሪ ሁኔታዎችን እንዲያሟላ ሊገደድ ይችላል።

፲፩· <u>ስለ ድጋፍ</u>

፩· ባንኩ ተገቢ ነው ብሎ ሲያምንበት ማናቸውም አነስተኛ ብድር አቅራቢ የገንዘብ ድርጅት በሚቋቋምበት ወይም ሥራውን በሚያካሂድበት ወቅት የሚጠይቀውን ቴክኒካዊ ድጋፍ ይሰጣል።

፪· አነስተኛ ብድር አቅራቢ የገንዘብ ድርጅቶች መልሶ ለማበደር ወይም ለካፒታል ማስፋፊያ የሚያውሉት የብድር አገልግሎት ወይም ማናቸውንም እርዳታ ከውጪ ሀገር ለማግኘት ይችላሉ።

፫· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት የሚገኝ ብድር ወይም እርዳታ በቅድሚያ የገንዘብ ሚኒስቴርን ይሁንታ ማግኘት አለበት።

<u>ክፍል ሦስት</u>

<u>የፋናንስ ግዴታዎችና ደንቦች</u>

፲፪· <u>ዝቅተኛ የካፒታል መጠን፣ የባንኩ ሥልጣንና ተግባር</u>

፩· አነስተኛ ብድር ለማቅረብ ሥራ ፈቃድ ለማግኘት የሚጠየቀው ዝቅተኛ የተከፈለ ካፒታል መጠን ባንኩ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል።

፪· ባንኩ ከዚህ የሚከተሉትን ጉዳዮች በሚመለከት መመሪያዎችን ለማውጣት ይችላል፣

ሀ) አነስተኛ ብድር አቅራቢ የገንዘብ ድርጅቶች ለማንኛውም ግለሰብ ወይም ቡድን ስለሚሰጡት ከፍተኛ የብድር መጠን፣

ለ) ስለብድር መክፈያ ጊዜና የአሰጣጥ ሥነ ሥርዓት፣

ሐ) ስለወቅታዊ ሪፖርት አቀራረብ፣ የሂሳብ አያያዝ ዘዴ እና የሂሣብ መዝገብ አያያዝ ሥርዓት፣

መ) ብድርን አስመልክቶ በየጊዜው ስለሚደረግ ጥቅል ምርመራና ስለኦዲት፣

ሠ) ስለተጠያቂነት፣ ስለመዋቅር፣ ስለቁጠባ ዘዴና ስለገንዘብ ክንውን ደረጃዎች ፣ እና

ረ) ለአነስተኛ ብድር አቅራቢ የገንዘብ ድርጅቶች ስለሚውል ልዩ የወለድ ተመን አወሳሰን።

፫· ባንኩ ከዚህ የሚከተሉትን የማከናወን ኃላፊነት አለበት፣

ሀ)ባንኮችና ሌሎች የገንዘብ ድርጅቶች አነስተኛ ብድር በማቅረብ ሥራ ላይ እንዲሳተፉ ወይም በዚህ መስክ ሥራቸውን እንዲያስፋፉ ማበረታታት ፤

ለ)ለአነስተኛ ብድር አቅራቢ የገንዘብ ድርጅቶች ሠራተኞች ሥልጠና መስጠት ወይም ሥልጠና እንዲያገኙ ሁኔታዎችን ማመቻቸት፤

4) where it is amalgamated with another micro financing institution or bank without prior written authorization of the Bank; or

5) where confirmed that its registration was effected on the basis of false information.

*10. Application for re-Registration*

1) where the savings mobilized by a micro financing institution equals Birr 1,000,000 (one million Birr) it shall apply for re-registration.

2) where application is made under sub-Article (1) of this Article, it may be required that additional conditions prescribed by directives issued by the Bank be met.

*11. Assistance*

1) Where it deems it appropriate, the Bank shall extend technical assistance requested by a micro financing institution while being organized or in the course of operations.

2) Micro financing institutions may obtain line of concessional credit or any assistance from foreign sources for the purpose of on-lending or capitalization.

3) Any credit or assistance to be obtained under sub-Article (2) of this Article shall require the prior approval of the Ministry of Finance.

PART TF

*Financial Requiremen. .d Limitations*

*12. Minimum Capital Requirement and Powers and Responsibilities of the Bank*

1) The minimum paid-up capital required to obtain license for micro financing business shall be determined by directives to be issued by the Bank.

2) The Bank may issue directives governing the following:

(a) limits on the maximum credit extended by micro financing institutions to any individual or group;

(b) the loan period and procedures;

(c) periodic reporting, the accounting system and the keeping of books of accounts;

(d) periodic surveys of loan and audits;

(e) standards regarding accountability, structure, savings system and financial performance;

(f) setting of special interest rate applicable to micro financing institutions.

3) The Bank shall have the responsibility to:

(a) encourage banks and other financing institutions to engage in micro financing business or to expand their activities in same;

(b) offer or facilitate training for the personnel of micro financing institutions;

ሐ) ዝቅተኛ ገቢ ያለው የኅብረተሰቡ ክፍል የበለጠ ጥቅም እንዲያገኝባቸው፣ እንደ እቁብ የመሳሰሉ ባሕላዊ የቁጠባ ተቋሞችን ማበረታታትና ማዳበር፤

መ) በሕግ በተሰጠው ሥልጣን መሠረት አነስተኛ ብድር በማቅረብ የሥራ መስክ ላይ የሚውለው ኢንቨስትመንት በተለይ በገጠሪቱ ኢትዮጵያ እንዲያድግ ማድረግ።

፲፫· <u>መጣመርና መቀላቀል</u>

በተጎራባች አካባቢዎች የሚንቀሳቀሱ የአነስተኛ ብድር አቅራቢ የገንዘብ ድርጅቶች መጣመርና መቀላቀል የሚበረታታ ይሆናል፤ ባንኩም ተገቢ ነው ብሎ የሚያምንበትን ማበረታቻ ለእንዲህ ዓይነቶቹ ድርጅቶች ይሰጣል።

፲፬· <u>ቅርንጫፎችን ስለመክፈት</u>

፩· ማናቸውም አነስተኛ ብድር አቅራቢ የገንዘብ ድርጅት ቅርንጫፉ ሥራውን በጀመረ በአሥራ አምስት (፲፭) ቀናት ውስጥ የቅርንጫፉን መከፈት ማሳወቅ አለበት።

፪· አነስተኛ ብድር አቅራቢ የገንዘብ ድርጅት ቅርንጫፍ ቢሮዎችን ስለሚከፍትበትና ሥራቸውን ስለሚያካሂድበት ሁኔታ ባንኩ አጠቃላይ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል።

<u>ክፍል አራት</u>

<u>ጠቅላላ ሁኔታዎች</u>

፲፭· <u>የብድር አገልግሎት አሰጣጥ</u>

አነስተኛ ብድር አቅራቢ የገንዘብ ድርጅቶች ለአባላትና አባል ላልሆኑም ብድር ሊሰጡ ይችላሉ። ሆኖም በቡድን ዋስትና የሚካሄዱ የብድር መርሀ–ግብሮች፣ተበዳሪዎችን የድርጅቶቹ አባል ለማድረግ መጣር ይኖርባቸዋል።

፲፮· <u>መሠረታዊ የጥንቃቄ ሥርዓት</u>

አነስተኛ ብድር አቅራቢ የገንዘብ ድርጅቶች በአጠቃላይ ሊከተሉት የሚገባ መሠረታዊ የጥንቃቄ ሥርዓት ባንኩ በሚያወጣው መመሪያ የሚወሰን ይሆናል።

፲፯· <u>ክልከላዎች</u>

ከባንኩ በቅድሚያ ይሁንታ ካላገኘ በስተቀር ማናቸውም አነስተኛ ብድር አቅራቢ የገንዘብ ድርጅት ፤

፩· በመቀላቀል ወይም በሌላ በማናቸውም መንገድ የንግድ ሥራውን መሸጥ ወይም የባለሀብትነት መተላለፍን የሚያስከትሉ ማናቸውንም ዓይነት ስምምነቶች ወይም ውሎች ማድረግ ወይም አወቃቀሩን መቀየር ፤

፪· በመደበኛ የሥራ ተግባሩ አፈጻጸም ካልሆነ በስተቀር ንብረቱን በሙሉ ወይም በከፊል በኢትዮጵያ ውስጥም ሆነ በውጭ ሀገር ለሌላ ሰው ማስተላለፍ ወይም በሌላ መንገድ ባለቤትነቱን ማዛወር ፤

፫· የካፒታሉን መጠን መቀነስ፣ ወይም

፬· የመመስረቻ ጽሑፉን ማሻሻል ወይም ሥራውን እንዲያካሂድ ፈቃድ ያገኘበትን ስም መቀየር ፤

አይችልም።

፲፰· <u>ለሥራ መሪነት ፈቃድ ስለሚያስፈልግበት ሁኔታ</u>

ከዚህ በታች የተመለከቱት ዓይነት ግለሰቦች ከባንኩ በቅድሚያ በጽሑፍ ካልተፈቀደላቸው በስተቀር ፣ የአነስተኛ ብድር አቅራቢ የገንዘብ ድርጅትን ሥራ ለመምራት አይችሉም፤



(c) promote and develop traditional savings institutions such as Iqub inorder that the low-income section of society benefit most from them; and

(d) promote investment in micro financing business, especially in rural Ethiopia, pursuant to powers vested in it under the law.

*13. Consolidation and Merger*

Consolidation and merger of micro financing institutions operating in adjacent areas shall be encouraged and such incentives as the Bank deems appropriate shall be granted to them.

*14. Opening of Branches*

1) Every micro financing institution shall notify its having opened a branch office, within fifteen (15) days of the commencement of operation of such branch.

2) The Bank may set general guidelines on donations of opening and operating branch offices by micro financing institutions.

PART FOUR

*General Conditions*

*15. Extending of Loan Services*

Micro financing institutions may extend loan to members as well as to non-members. However, such credit schemes as operating under group guarantee shall exert themselves to bring borrowers into membership of the institutions.

*16. Minimum Operational Prudence*

The minimum prudential framework of operation in respect of all micro financing institutions shall be in the manner and form to be prescribed by the Bank.

*17. Prohibitions*

Without the prior approval of the Bank no micro financing institution may:

1) enter into any arrangement or agreement for the sale or disposal by amalgmation or otherwise of its business or effect self restructuring;

2) transfer or otherwise dispose of the whole or any part of its property, whether inside or outside Ethiopia, other than in the ordinary course of its business;

3) effect reduction of its capital; or

4) amend its memorandum of association or alter the name under which it is licensed.

*18. Circumstances Requiring Approval for Managerial Responsibility*

The following shall not be allowed to manage micro financing institutions without the prior written approval of the Bank:

፩· በኢትዮጵያ ውስጥም ሆነ በውጭ ሀገር የመክሰር ውሳኔ የተሰጠባቸው ወይም ስለኪሳራው ከገንዘብ ጠያቂዎቻቸው ጋር ስምምነት ያደረጉ፣ ወይም

፪· በኢትዮጵያ ውስጥም ሆነ በውጭ ሀገር እምነት በማጉደል ወይም በአታላይነት ወንጀል የተፈረደባቸው።

፲፱ <u>የግብር ነፃነት</u>

አነስተኛ ብድር አቅራቢ የገንዘብ ድርጅቶች ከገቢ ግብር ነፃ የሚሆኑበትን ጊዜና አፈጻጸሙን የመወሰን ሥልጣን በዚህ አዋጅ ለገንዘብ ሚኒስቴር ተሰጥቶታል።

፳· <u>ልዩ ኃላፊነት</u>

ማናቸውም አነስተኛ ብድር አቅራቢ የገንዘብ ድርጅት ዝቅተኛ ገቢ ያለው የኅብረተሰብ ክፍል፣ በተለይም በገጠር አካባቢዎች፣ ብድር ሊያገኝ የሚችልበትን ፖሊሲ በማውጣት መፈጸም እና ለዚሁም ዓላማ የቡድን ዋስትና የንብረት ዋስትናን የሚተካባቸውን መንገዶች ሥራ ላይ ማዋል ይኖርበታል።

<u>ክፍል አምስት</u>
<u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

፳፩· <u>የመተባበር ግዴታ</u>
ይህን አዋጅ ሥራ ላይ በማዋል ረገድ ባንኩ ሲጠይቅ የሚመለከታቸው አካላት የመተባበር ግዴታ አለባቸው።

፳፪· <u>ስለ ሂሳብ ምርመራ</u>

ማናቸውም አነስተኛ ብድር አቅራቢ የገንዘብ ድርጅት ከተጣራ ዓመታዊ ትርፉ ላይ ለባለአክስዮኖቹ ከማከፋፈሉ በፊት ሂሳቡ በባንኩ ተቀባይነት ባለው ነፃ ኦዲተር መመርመር አለበት።

፳፫· <u>ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸው ሕጎች</u>
ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረኑ ሕጎች በዚህ አዋጅ የተሸፈኑ ጉዳዮችን በተመለከተ ተፈጻሚነት አይኖራቸውም።

፳፬· <u>ተፈጻሚነት ስላለው ሌላ ሕግ</u>
በዚህ አዋጅ ባልተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ የባንክ ሥራ ስለመፍቀድና ስለመቆጣጠር የወጣው አዋጅ ቁጥር ፹፬/፲፱፻፹፮ እንዳስፈላጊነቱ እየተቃና ተፈጻሚ ይሆናል።

፳፭· <u>መመሪያ የማውጣት ሥልጣን</u>

ባንኩ ይህን አዋጅ በሚገባ በሥራ ላይ ለማዋል መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል።

፳፮· <u>የመሸጋገሪያ ድንጋጌ</u>

፩· ይህ አዋጅ ከመጽናቱ በፊት አነስተኛ ብድር በማቅረብ ሥራ ላይ የተሰማሩ ድርጅቶች ከአዋጁ ድንጋጌዎች ጋር በሚጣጣም መልኩ እስኪዋቀሩ ድረስ በነበሩበት ሁኔታ ሊቀጥሉ ይችላሉ።

፪· አዋጁ በተጠቀሱት ድርጅቶች ላይ ተፈጻሚ ሳይሆን ሊቆይ የሚችልበት ሁኔታና የጊዜ ገደብ ባንኩ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ይወሰናል።

1) persons declared bankrupt or who have made a compromise with their creditors, whether in Ethiopia or elsewhere;

2) persons convicted of offences of breach of trust or fraud, whether in Ethiopia or elsewhere.

*19. Tax Exemption*

The Ministry of Finance is hereby empowered to determine the period, manner and condition of exemption of micro financing institutions from income tax.

*20. Special Responsibility*

Every micro financing institution shall devise and execute a policy whereby the low-income section of society, especially in rural areas, get access to credit and to this end it shall implement such means of substituting group guarantee for property collateral requirement.

PART FIVE

*Miscellaneous Provisions*

*21. Duty to Cooperate*

Where so requested by the Bank, all concerned bodies shall have the duty to cooperate in the implementation of this Proclamation.

*22. Audit*

Accounts of micro financing institutions shall be audited annually by an independent auditor acceptable to the Bank prior to the payment of dividends to shareholders.

*23. Inapplicable Laws*

Any law inconsistent with the provisions of this Proclamation shall not apply to matters provided for under this Proclamation.

*24. Other Applicable Law*

With respect to matters not covered under this Proclamation, the Licensing and Supervision of Banking Business Proclamation No. 84/1994 shall apply, mutatis mutandis.

*25. Power to Issue Directives*

The Bank may issue directives necessary for the proper implementation of this Proclamation.

*26. Transitory Provisions*

1) Undertakings engaged in micro financing business, prior to the coming into force of this Proclamation, may continue in their previous form until reorganized in compliance with the provisions of this Proclamation.

2) The conditions and time limit of non-applicability of this Proclamation to such undertakings shall be determined in directives to be issued by the Bank.

፳፯. አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ
ይህ አዋጅ ከሰኔ ፳፰ ቀን ፲፱፻፹፰ ዓ.ም. ጀምሮ የጸና ይሆናል።

አዲስ አበባ ሰኔ ፳፰ ቀን ፲፱፻፹፰ ዓ.ም.

ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ፕሬዚዳንት

27. *Effective Date*
This Proclamation shall come into force as of the 5th day of July, 1996.

Done at Addis Ababa, this 5th day of July, 1996.

NEGASO GIDADA (DR.)

PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC

REPUBLIC OF ETHIOPIA

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ
BERHANENA SELAM PRINTING ENTERPRISE